# የACPS Express 1/27/2023: የACPS ትምህርት ቤት፣ የምግብ ማቅረቢያው(Food Pantry)ን - የማህበረሰብ-ፍላጎቶችን ለማገዝ ክፍት-አድርጓል

## የACPS ትምህርት ቤት፣ የምግብ ማቅረቢያውን - የማህበረሰብ-ፍላጎቶችን ለማገዝ ክፍት-አድርጓል



*የጆርጅ ሜሰን (George Mason) ትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (Social Worker) - ኦድሪ ሮቢንሰን (Audrey Robinson)፣ የሴሪያል ካርቶኖች (cereal boxes)ን - በሜሰን ገበያ (The Mason Market) ላይ ሲያዘጋጁ።*

የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (social worker) - በምግብ ዋስትና-ማጣት እየተቸገሩ ያሉ ቤተሰቦችን ለመርዳት ውሳኔያቸውን በማድረግ፤ ያላቸውን ራዕይ ወደ እውነታው የቀየሩት - የምግብ ማቅረቢያ (food pantry)ን በጆርጅ ሜሰን (George Mason) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በማስጀመር-ነው። ኦድሪ ሮቢንሰን (Audrey Robinson) - የምግብ-ማቅረቢያ (food pantry) ሃሳቡን-ያመጡ ሲሆን፣ በሮቻቸውን በዲሴምበር (December) 2022 ላይ ከፍተዋል። ርዕሰ መምህር ዶ/ር ሲዛንቴ ኦሊቨር (Dr. Seazante Oliver) - ስሙ፣ 'The Mason Market' እንዲሆን መርጠዋል። ከአሊሲአ አልስተን-ሃሪስ (Alicia Alston-Harrison)፣ ከጀስቲን ውድ (Justin Wood) እና ከርቲስ ዶኖሁዌ (Curtis Donohue) እርዳታ-ጋር በመሆን፤ ይህ የምግብ ማቅረቢያ (pantry)፣ አሁን የ[Capital Area Food Bank](#) ፓይለት-ፕሮጀክት (pilot project) አንዱ-አካል በመሆን፣ የምግብ መገኛ ምንጮችን በአካባቢው ትምህርት ቤቶች ውስጥ በማቅረብ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ፍላጎቶች ምላሽ-በመስጠት ለመርዳት የሚያቅርብ-ነው። የጆርጅ ሜሰን ማህበረሰብ ለሁሉ-ተደራሽ (The George Mason Community Outreach) ኮሚቴም፤ ይህን ትልቅ-የሆነ ፕሮጀክትን የሚደግፍ-ነው።

ዶ/ር ኦሊቨር (Dr. Oliver) እንዳሉት፤ ዓላማው - ለሁሉም ልጅ እንክብካቤ እና እርዳታ ለማድረግ እና ይህም የሚያካትተው የምግብ-ዋስትና አለማግኘት ላይ ምላሽ-መስጠትን ነው። የትምህርት-አሰጣጥን ማግኛ፣ የማህበራዊ-ስሜታዊነት እርዳታ፣ እና ወደ እነዚህ የመገኛ-ምንጮች የማግኘት አቅም እንዲኖር ነው የምናስበው፤ ነገር ግን መሠረታዊ-የሆነ የሰው-ልጅ ፍላጎቶች አሉ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የተወሰነ ምግብ መገኘት እንዲችል ማድረግ ያስፈልገናል - ይህም በጣም አስፈላጊ-ነገርም ነው" ብለዋል ዶ/ር ኦሊቨር (Dr. Oliver)።

"የተራበ ሆድ - ለመማር የተመቻቸ-አይሆንም፣" ብለዋል ሮቢንሰን (Robinson)። አልስተን-ሃሪስ (Alston-Harrison) ጨምረው-ሲናገሩ፤ "የምግብ-ማቅረቢያው (The pantry) - ስጦታ-የመስጠት፣ ምግብ የማቅረብ፣ ጊዜያችሁን የመስጠትና ሌሎችን የመርዳት - ምሳሌ ነው።"



*የጆርጅ ሜሰን ትምህርት ቤት ካውንስለር - አሊሲአ አልስተን-ሃሪስ (Alicia Alston-Harrison) እና የጆርጅ ሜሰን ትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (Social Worker) ኦድሪ ሮቢንሰን (Audrey Robinson)፤ የ'The Mason Market' ህይወት-እንዲያገኝ*

*ረድተዋል። በፎተግራፉ-ላይ የሌሉት - ከርቲስ ዶኖሁዌ (Curtis Donohue) እና ጀስቲን ውድ (Justin Wood) - በዚህ ጥረት-ላይ ዋነኛውን ሚና የተጫወቱ-ናቸው።*

የ'The Mason Market' የሚገኘው - በመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲሆን፣ ስብጥር-ያላቸውን የምግብ-ዓይነቶች - ዶሮ እና ትኩስ ምርትን ጨምሮ - እንደ አፐሎች (apples)፣ ስኳር-ድንች (sweet potatoes) እና ሽንኩርት (onions) ያሉትን ይሰጣል። መደርደሪያ ሼልፉም፤ እንደ ሴሪያል (cereal)፣ ሾርባ (soup)፣ ጭማቂ (juice)፣ ሩዝ፣ እና ባቄላዎች (beans) ያሉ በምግብ ባንክ የቀረቡ እና ከማህበረሰቡ በልገሳ-የተሰጡትን የያዘ-ነው። ማንኛውም የሚያስፈልገው-ሰው መመዝገብ የሚችል እና የምግብ ማቅረቢያው (food pantry)ን ማግኘት-ይችላሉ።

ዶ/ር ኦሊቨር (Dr. Oliver)፤ የ'The Mason Market'ን፣ የማህበረሰብ-ፕሮጀክት ብለው-ጠርተውታል። "እኛ-አሁን እንደ ትልቅ-ቤተሰብ የሆንን፣ በከፍተኛ-ሁኔታ - በትምህርት ቤታችን እና በማህበረሰቡ እና በ'Capital Area Food Bank' መካከል-አጋርነትን የፈጠርን-ነን፤" ብለዋል። "ይህ-የእኛ የመጋቢነት... ጊዜን፣ ተሰጥዖን እና ጥረትን መስጠት፣ እና ይህንን-ነው ቡድናችን ያደረገው፣" ብለው-ጨምረዋል ሮቢንሰን (Robinson)።



የ'The Mason Market' - በመደበኛነት፤ በሣምንት ሁለት-ጊዜ፤ በሚከተሉት ጊዜያቶች ክፍት-ነው: ረቡዕ-ዕለታት ከ3-5 p.m.፤ እና አርብ-ዕለታት ከ9-11 a.m። ከሜሰን የወላጅ አስተማሪ ማህበር (Mason Parent Teacher Association (PTA) ጋር በመተባበር፣ የምግብ-ማቅረቢያው (food pantry) - በተጨማሪም በፒቲኤ (PTA)' ስብሰባ ምሽቶች ላይ ከ7-8:30 p.m. ክፍት-ናቸው። የትምህርት ቤት ሠራተኞች፤ መጓጓዣ በማዘጋጀት እና ምግብን በቀጥታ ወደ ቤተሰቦች በማድረስም እርዳታ-ያደርጋሉ።

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች Alexandria City Public Schools (ACPS) - የትምህርት ቤት የማህበራዊ ስራ ዳይሬክተር — ፋይዛ ጃክሰን (Faiza Jackson) ሲናገሩ፣ የጆርጅ ሜሰን የምግብ ማቅረቢያ (George Mason food pantry) ተከፍቶ-እና እንቅስቃሴውን-እያካሄደ ባለበት ጊዜ፤ ከ'Capital Area Food Bank' ጋር በመሆን፤ የጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤትን - እንደ ሁለተኛ የፓይለት የምግብ ማቅረቢያ ፕሮግራም ቦታው (second pilot food pantry program site) ተደርጎ-ተመርጧል።  ይህ የሞዴል ስራ ስኬታማ ከሆነ፤ በክልሉ ዙሪያ፣ የምግብ-ማቅረቢያዎችን በትምህርት ቤቶች ውስጥ በመገንባት - ቤተሰቦች ቀጣይነት-ባለው አሰራር ምግብ-ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ፤ የምግብ ባንክ ዕቅዶቹን የሚያስፋፋ-ይሆናል።

የምግብ-የመገኛ ምንጮች፤ በአሁኑ-ጊዜ በሌሎች መንገዶች በACPS ትምህርት ቤቶች ውስጥም የሚሰጡ-ናቸው። ለምሳሌ፤ ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከK-8 ትምህርት ቤት - በትምህርት ቤት ጊቢው ውስጥ - ለማህበረሰቡ በቀን 24 መገኘት የሚችል የምግብ-ማቅረቢያ (pantry box) አለው። ይህም፤ በማርችአንድ ቤተሰብ (Marchand family) የተጀመረው -  [Be The Good] ተብሎ-የሚጠራው ድርጅት - በየቀኑ የምግብ-ማቅረቢያን በመሙላት እርዳታ በመስጠት እና በመገንባት - ያደረገው-ጥንካራ ጥረቶች ውጤት-ነው። በተጨማሪም፤ ድርጅቱ ለፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከምግብ-ጥቅል ቦርሳዎች ጋር ቁሳቁሶችን የሚያቀርግ ሲሆን፣ ይህም የ$25 የግሮሰሪ የስጦታ ካርዶች (gift cards)ን በመስጠት፤ ቶሎ የሚበላሹ ነገሮችን ለመግዛት እንዲጠቀሙበትን ያደርጋል።

የምግብ-ማግኛ ምንጮች በሌሎች የACPS ቦታዎች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ ይገኛል:

- ኮራ ኬሊ (Cora Kelly) ትምህርት ቤት ለሂሳብ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ - እንደ  [ALIVE!] ለአጭር-ጊዜ ብቅ የሚሉ የምግብ ማከፋፈያ-ቦታዎች (pop-up food distribution point) ሆኖ ያገለግላል።

- የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት - ወርሃዊ የማህበረሰብ ገበያ - ከምግብ ማከፋፋያ ጋር በ'Capital Area Food Bank' አካባቢ-ይኖረዋል።
- የማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት - የ[Blessings in a Backpack](#) ፕሮግራምን ያቀርባል።
- የዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወርሃዊ የምግብ ማከፋፈያዎች - ለቤተሰቦች ያለው ሲሆን፤ በእያንዳንዱ ወር በሁለተኛው ማክሰኞ-ላይ (በጁን/June ወር ውስጥ ብቻ በወሩ የመጨረሻ-ማክሰኞ ከሚሰጠው-በስተቀረ) ከ'Capital Area Food Bank' ከሚገኝ-እርዳታ ጋር ምግቦችን-ያከፋፍላል። በተጨማሪም፤ የ'ALIVE!' ለአጭር-ጊዜ ብቅ የሚሉ የምግብ ማከፋፈያ-ቦታዎች (pop-up food distribution) - ከትምህርት ቤቱ የመዝናኛ ማዕከል ላይ ሆኖ አገልግሎት-ይሰጣል።

## የACPS—ጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) ዩኒቨርስቲ፣ አጋርነት - የACPS የልዩ ትምህርት-ሰጪ (Special Education) አስተማሪዎችን ቁጥርን በማስፋት ላይ-ዓላማ ያደረገ የተነሳሽነት ፕሮራምን አስጀምረዋል

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ከጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ (The George Washington University's (GW) የ'Graduate School of Education and Human Development' ጋር አጋርነትን-በመፍጠር፤ በልዩ-ትምህርት አሰጣጥ ላይ እገዛ-ሰጪዎችን እና አስተማሪዎችን - በACPS ውስጥ ከpreK-12 ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፤ በ18 ትምህርት ቤቶች ውስጥ - ያለውን ቁጥር ለማስፋፋ የተነሳሽነት ስራን እያስጀመረ-ነው። ግለሰቦች፤ በአንድ-ጊዜ ወደ ሁለቱም ወደ 'GW የmaster's ፕሮግራም እና በACPS ውስጥ ቅጥር-ለማግኘት በሁለቱም-ማመልከት ይችላሉ። በመጀመሪያ ዓመት ፕሮግራማቸው ውስጥ እያሉ፣ ተመራቂ-ተማሪዎች (graduate students)፣ እንደ ACPS የትምህርት-አሰጣጥ ረዳቶች ሆነው - ቁልፍ የሆኑ የትምህርት አሰጣጥ ስልቶችን እንዲቀርጹ፣ ተመራጭ-የሆነው የአሰራር መንገድ እንዲማሩ እና ዒላማ-የተደረገበት የባለሙያተኝነት መማርን - ከሁለቱም ለACPS እና GW ቡድኖች ማግኘት-እንዲችሉ ሆነው የሚሰሩ-ይሆናል። በሁለተኛ ዓመት ፕሮግራማቸው ውስጥ - በመቀጠልም እንደ የአስተማሪነት ሚናዎችን በመጫዎ እንዲሰሩ ዕድልን ያገኛሉ። ACPS - በትምህርት-መማሪ ክፍያዎች ላይ እርዳታ እንዲያደርግ በየዓመቱ፤ የ$800 የገንዘብ እርዳታን ለእያንዳንዱ የፕሮግራም ተሳታፊዎች ለመስጠት በቁርጠኝነት-ይሰራል። በበጋ (summer) 2023 ላይ፣ የመጀመሪያዎቹን የጥምረት (cohort) ተማሪዎችን፤ ይህን ግብ እውን-ለማድረግ ሲባል፤ ፕሮግራሙ አመልካቾችን መመልመል ይጀምራል። [የ'ACPS የስራ-መስክ መረጃ (career information)፤ በኦንላይን መገኘት ይችላል](#)።

"ከጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ (George Washington University) የ'Graduate School of Education and Human Development' ጋር አዲስ-አጋርነትን በመጀመር - እንደ በልዩ ትምህርት (special education) ውስጥ እንደ የስራ-መስክ ፍላጎትን-እንዲኖር የመጨመሪያ መንገድን-በመፈለግ፤ እና በACPS ውስጥ ብቃት-ያላቸውን አስተማሪዎች ለመጨመር-ይህን አጋርነት ስለፈጠርን በጣም-ደስ ብሎናል" ብለዋል - የACPS ጊዜያዊ ጠቃላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)። "ሁሉንም ተማሪዎች ለማገልገል በምንሰራበት-ጊዜ፣ ከፍተኛ-ብቃት በልዩ ትምህርት አስተማሪነት ያላቸውን ለመለየት የሚያስችል አዲስ መንገዶችን መፈለጋችንን መቀጠል - በጣም አስፈላጊ-ነው። እኔ-እራሴ የቀድሞ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ እንደመሆኔ፤ ለተመራቂ ተማሪዎች (graduate students) በእንደዚህ ዓይነት ፕሮግራም ውስጥ መሳተፋቸው - በመማሪያ-ክፍሎቻቸው ውስጥ ከሚገባ-ለመስራት የሚያስፈልጋቸውን - ጠንካራ ስልጠና እና በእውን-ያለውን ተሞክሮዎች እንዲያገኙ እንደሚረዳቸው አውቃለሁ።"

ፕሮግራሙ - የማስተርስ ዲግሪያቸውን በትምህርት/education  የሚያገኙ የ'GW graduate students'፤ ስለ ACPS የስራ-መስክ ዕድሎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና በልዩ ትምህርት (special education) ውስጥ ፍላጎት-ያላቸው የትምህርት ቤት ክፍል ሠራተኞች፤ ስለ 'GW graduate program' መረጃ-ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ-ይሆናል። የመጀመሪያው ምልመላ - ዌቢናሮችን እና ቁሳቁሶች (webinars and materials)ን የሚሰጥ ሲሆን - በአሁኑ ጊዜ በACPS ውስጥ እንደ ትምህርት አሰጣጥ እርዳታ-ሰጪዎች ሆነው፣ እንደ ተተኪ አስተማሪዎች (substitute teachers)፣ እና ሌላ የሠራተኛ የስራ-ድርሻዎች ይዘው የሚሰሩት - የ'advanced degree'ን በ'GW' ውስጥ ማግኘትን ከግምት-ውስጥ እንዲያስገቡ እና በACPS ውስጥ በልዩ ትምህርት (special education) የበለጠ-ከፍያ ወዳለው የማስተማር የስራ-ድርሻ ብቁ-እንዲሆኑ - ለማድረግ የሚሰጥ-ይሆናል።

"የACPS-GW አጋርነት፤ በጠንካራ፣ ለከፍተኛ ብቃት ያለው የልዩ ትምህርት አስተማሪዎች በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ በአስቸኳይ የማስፈለግ ችግርን ለመፍታት ባለው የጋራ-ቁርጠኝነት ምክንያት-የተመሠረተ ነው፤" ብለዋል - የ'GW' የልዩ ትምህርት እና የጉዳተኝነት ጥናት መምሪያ ሊቀመንበር እና አስተባባሪ ፕሮፌሰር (Special Education & Disability Studies Department Chair and Associate Professor) - ዶ/ር ቤት ተከዊለር (Dr. Beth Tuckwiller)። "አጋርነት ያለው የአስተማሪ ዝግጅት የአጋርነት-ስራችን፣ አስተማሪዎች ለመሆን ባለሙያተኝነት ያለው የስራ-መስክ መንገድን ይፈጥራል፣ የGW pre-service አስተማሪዎችን - ከፍተኛ-የሆነ ስም ባላቸው የአካባቢው የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ ዕድሎችን እንዲያገኙ ያገናኛል፣ እና ሁሉን-አቀፍ የሆነ፣ ከፍተኛ-ደረጃ ያለው የአስተማሪ ዝግጅት ተሞክሮን - ውጤታማ የሆነ መንገዶችን በጠንካራ-ጎኖች እና በመገኛ-ምንጮች ላይ ለሁለቱም አጋሮች በመጠቀም - ጠንካራ-የሆነ እና ቋሚነት ያለው የአስተማሪ መገኛ-መንገድን ይፈጥራል።  ከACPS ጋር በመተባበር - ከፍተኛ-ችሎታዎች ያሏቸው፣ እውቅት-ያዳበሩ፣ እና ምላሽ-ሰጪ አስተማሪዎችን - በአካባቢው የሚገኙ ተማሪዎችን እና ቤተሰቦቻቸውን እንዲያገለግሉ ለማዘጋጀት ዕድል በማግኘታችን በጣም-ደስተኞች እና ምስጋና የምናቀርብ-ነን።"

ACPS - መረጃ-ሰጪ የሆነ ዝግጅትን በፌብሩዋሪ (February) ወር መጀመሪያ ላይ የሚያዘጋጅ ሲሆን፣ ይህም ለሁሉም ፍላጎት-ላላቸው ግለሰቦች - በአሁኑ ጊዜ የACPS ተቀጣሪ-ሠራተኞችን እና የ'GW' ተማሪዎችን ጨምሮ ሊሳተፉበት የሚችሉ-ይሆናል። ይህን አስደሳች ዕድል በማግኘት ለመቀጠል ፍላጎት ያለው ማንም-ሰው፤ በACPS ድህረ-ገጽ አማካኝነት - ልዩ የስራ-ማስታወቂያዎች የሚኖሩት፣ እና በፌብሩዋሪ (February) 2023 መረጃ-ሰጪ ዝግጅት ወቅት ላይ በሚኖር ማመልከቻ-ማመልከት ይቻላል። የACPS እና የ'GW' ቡድኖች፤ በአንድነት-ሆነው - ለመጀመሪያ ጥምረት እና የጋራ ፕሮግራም ገብተው-ለመማር (first cohort and share program enrollment) ብቁ የሆኑ አመልካቾችን የሚወሰድ ውሳኔዎችን - እስከ ማርች (March) 2023 መጀመሪያ-ድረስ ያደርጋሉ። የጥምረት አባላቶቹ (Cohort members)፤ የኔትወርክ እና የቃለ-መጠይቅ ዝግጅቶችን - የቅጥር-ሂደቱን ለማካሄድ፣ በፀደይ (spring) 2023 ወቅት-ሙሉ፣ ከACPS የትምህርት ቤት አመራሮች ጋር እንዲካፈሉ የሚጋበዙ፤ እና እንዲጀምሩ የሚጠይቅ ደብዳቤዎች (offer letters) እስከ ጁን (June) 2023 ድረስ ባለው-ጊዜ የሚሰጥ-ይሆናል።

ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት፤  የACPS የፕሬስ መግለጫ - ስለአጋርነት የሚያስተዋውቀው - በኦንላይን ላይ የሚገኝ-ይሆናል።

## ጃንዋሪ (Jan.) 30 ቀን 2023፤ የትምህርት ቤት ቦርድ የቋንቋ የአድቫይዘሪ ኮሚቴ (Language Advisory Committee) - ፍላጎት-ያላቸው ስብሰባ




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤት (Alexandria City Public School) ቦርድ - በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ - የተለየ የቋንቋ ፍላጎቶች ላሉዋቸው ድምጽ-ሆኖ እርዳታ የሚያደርጉ፤ የስፓኒሽ-፣ አማርኛ-፣ እና አረብኛ- ቋንቋ ተናጋሪ አድቫይዘሪ ኮሚቴዎችን እያቋቋመ-ነው። ፍላጎት ላላቸው የACPS የማህበረሰብ አባላቶች - የመጀመሪያ የርቀት (virtual) ስብሰባውን - ወላጆች/አሳዳጊዎችን ጨምሮ፤ በዙም(Zoom) አማካኝነት - በ6 p.m. ላይ፣ ሰኞ፣ ጃንዋሪ (Jan.) 30 ቀን 2023 ያካሂዳል። የትምህርት ቤት ቦርድ አባላቶች - ይህን ስብሰባ የሚያስተናብሩ ይሆናል፣ እና ከእነዚህ ሦስት ቋንቋዎች አንዱን የሚናገር ማንኛውም የACPS የማህበረሰብ-አባል እንዲመጣና እንዲካፈል ይጋበዛል። በርቀት (virtual) ስብሰባው ላይ፣ በዙም/Zoom ለመካፈል - ምንም ምዝገባ አያስፈልግም፤ የቋንቋ ትርጉም-የሚሰጥ አስተርጓሚም ይኖራል (የስብሰባ መለያ ቁጥር (Meeting ID): 998 0849 3243; የመግቢያ ኮድ (Passcode): 241187).

ኮሚቴ አባላቶች፤ በትምህርት ዓመቱ ሙሉ - ትኩረት የተደረገባቸው-ነገሮችን በተመለከተ፣ ለእነዚህ ማህበረሰቦች አስፈላጊ-የሆኑ ርዕሶች ላይ - ከቤተሰብ ተሳትፎ ተመራጭ-የሆነ ልምዶች ጋር ጎን-ለጎን በመሆን - አስተያየት (feedback) ለማጋራት ዕድል ይኖራቸዋል። እነርሱም፤ ስፓኒሽ፣ አማርኛ እና አረብኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስለሚያስፈልጓቸው ነገሮች ለትምህርት ቤት ክፍሉን/school division ለማሳሰብ እንዲረዱ እና/ወይም የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማር (English Learner (EL) ወኪሎች እንዲኖራቸው የሚረዱ-ይሆናል። እነዚህ የተማሪ ቡድኖች፤ ACPS - እነዚህን ቋንቋዎች ለሚናገሩ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ስለሚሰጠው እርዳታ - ማህበረሰቡን በማስተማር-እየረዱ ባሉበት-ጊዜ፤ ስለነዚህ የተማሪ ቡድኖች ትምህርትን-በተመለከተ ያላቸውን ሃሳቦች-በመስጠትም ያቀርባሉ። ስብሰባዎቹ - በአፍ-መፍቻ ቋንቋዎች (native languages) እና ከእንግሊዘኛ-ቋንቋ የማስተርጎም-አገልግሎት ጋር የሚካሄዱ-ይሆናል።

በጃንዋሪ (Jan.) 30 ቀን 2023 የርቀት (virtual) ስብሰባው ላይ፣ ስለ ኮሚቴዎቹ ተጨማሪ ዝርዝር-መረጃዎች የሚጋሩ ይሆናል። ወደ እነዚህ የትምህርት ቤት ቦርድ የቋንቋ አድቫይዘሪ ኮሚቴዎች (Language Advisory Committees) ለመቀላቀል - የኦንላይን የማመልከቻ ቅጾች፤ በ እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ ወይም አረብኛ ይገኛሉ።

## መጪው - የፌብሩዋሪ (February) ወር - ክንውን: የማህበረሰብ ተሣትፎ እና የቀን-መቁጠሪያ (Calendar)፣ ማስታወሻዎች

Community Outreach
& CALENDAR REMINDERS

ለፌብሩዋሪ (February) ወር፤ ስለ የቀን-መቁጠሪያ (Calendar) ማስታወሻዎች እና ስለ መጪዎቹ የማህበረሰብ ዝግጅቶች፤ እወቁ። የACPS የማህበረሰብ ሁሉን-የሚያዳርስ (Community Outreach) ቡድን፤ በእናንተ አጎራባች-አካባቢ - መቼ እንደሚገኙ እወቁ!

## ESL II - የመነጋገሪያ ክለብ (Conversation Club)፣ ለመካከለኛ-ደረጃ (Intermediate) ‘ESL’ ተናጋሪዎች

**በፌብሩዋሪ (February) ወር ውስጥ - ዘወትር ሰኞ ቀናት፣ እና ሮብ ቀናት ላይ (ፌብሩዋሪ/Feb. 1, 6, 8, 13, 15, 20, 22, 27)፤ ከ5:30-6:30 p.m.**
**ቻርልስ ኢ. ቢትሊ (Charles E. Beatley Jr.) Central Library (5005 Duke St.)**
የአሌክሳንድርያ የመጽሐፍት-ቤት (Library)፤ የመማር፣ የመዳሰስ፣ የመፍጠር እና ግንኙነት-ማድረጊያ ዕድሎችን በመፍጠር - ማህበረሰብን ይገነባል። የ‘ESL II Conversation Club’፣ ለመካከለኛ-ደረጃ ላይ ያሉ ተናጋሪዎች (intermediate speakers)፣ እንግሊዘኛ ቋንቋን ልምምድ እንዲያደርጉ እና በራስ-መተማመናቸውን እንዲገነቡ የሚያገለግል-ቦታ ነው። ምዝገባ፣ አያስፈልግም።

## ለወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ቀደም-ብሎ መለቀቂያ (Early Release) ቀናቶች

**ሐሙስ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 2 እና አርብ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 3 ቀን (ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)**
**ሐሙስ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 9 እና አርብ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 10 ቀን (የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች - ከተከር (Tucker) በስተቀረ፤ እና ከK-8 ትምህርት ቤቶች)**
**ሐሙስ፤ ፌብሩዋሪ (Feb.) 16 እና አርብ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 17 ቀን (መካከለኛ ደረጃ/Middle ትምህርት ቤቶች)**
የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለቤተሰቦች እና አስተማሪዎች፣ ስለ ተማሪው የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የመማር ላይ - ስለሚያሳየው እድገት ለመወያየት፤ በጣም ጠቃሚ-የሆነ እዕድልን የሚሰጥ ነው። በፌብሩዋሪ (February) ወር ውስጥ፤ የትምህርት ቤት ኮንፈረንሶች በሚካሄደበት ጊዜ ውስጥ - ከተመደው የመለቀቂያ-ጊዜ “ቀደም ብሎ መለቀቂያ/early release” ቀናቶ የሚከናወኑ እና፣ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሁለት ሰዓታት ቀደም-ብለው ይለቀቃሉ። ለኮንፈረንሶቹ ስለመመዝገብ (sign-ups) በተመለከተ፤ እያንዳንዱ አስተማሪ - ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል።

## የ2023 ፍትሃዊ-እኩልነት ሁኔታ (Equity Climate) የዳሰሳ-ጥናት

**ከአርብ. ፌብሩዋሪ (Feb.) 3 ቀን - እሁድ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 26 ቀን ድረስ**
ሁሉም ቤተሰቦች፣ ሠራተኞች፣ እና ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ-ተማሪዎች፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 3 ቀን እና በፌብሩዋሪ (Feb.) 26 ቀን 2023 መካከል-ባሉት ቀናት፤ ይህን የዳሰሳ-ጥናት እንዲያጠናቅቁ ይጠየቃሉ። የአምስት-ዓመት ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan)፣ እኩልነት ለሁሉም (Equity for All) 2025 ወደፊት-እንዲገፋ በምንሰራበት ጊዜ፣ ስለ ACPS ትምህርት ቤት ያለው-ሁኔታ ምን እንደሆነ እና ስለ የመማሪያ አካባቢዎቹ - በማህበረሰባችን ውስጥ ስለአሉ በርካታ አመለካከቶች ለመስማት ደስታ-ይሰማናል።

## የእኛ ፊቶቻችን - በፊልም ውስጥ

**አርብ-ቀናቶች በፌብሩዋሪ (February) ውስጥ - (ፌብሩዋሪ/Feb. 3, 10, 17, 24)፤ ከ2-4:30 p.m.**
**ቻርልስ ኢ. ቢትሊ (Charles E. Beatley Jr.) Central Library (5005 Duke St.)**
የአሌክሳንድርያ የመጽሐፍት-ቤት (Library)፤ የመማር፣ የመዳሰስ፣ የመፍጠር እና ግንኙነት-ማድረጊያ ዕድሎችን በመፍጠር - ማህበረሰብን ይገነባል። ወሩን-ሙሉ የሚቆይ ለ‘Black History Month’፣ መጽሀፍት-ቤቱ - ስለ አአፍሪካዊ አሜሪካዊያን መሪ ገጸ-ባህሪያቶች (African American lead characters) የሚያሳዩ ፊልሞችን ያሳያል። ግሩም-የሆኑ ፊልሞችን በመመልከት እና ስናክ-እየበላችሁ፣ ከእኛ-ጋር ተቀላቀሉ!

## የACHS የቀለም-ትምህርት ማስተዋወቂያ (Orientation) & የስርዓተ-ትምህርት ምሽት (Curriculum Night)

**ሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 6 ቀን፤ ከ5:30-7:30 p.m.**
**የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - King Street Campus (3330 King St.)**

በአሁኑ-ጊዜ ከስምንተኛ ክፍል እስከ 11 ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ እና ቤተሰቦቻቸው፤ ግሩም-የሆነው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞቻችን ምን-እንደሆኑ አጭር-ምልከታ እንዲኖራቸው - ተጋብዘዋል። የዚህ ምሽት ፕሮግራም፤ ቤተሰቦች - በምርቃት መስፈርቶች፣ የሚሰጡት ኮርስ፣ ቅደም-ተከተል፣ እና የሚጠበቁ-ነገሮች ላይ- የሚሰጡትን ክፍለ-ጊዜዎች ለመካፈል ዕድል ይሰጣል። ልዩ የሆነ ክፍለ-ጊዜዎች - በሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ እና በሂሳብ (Science, Technology, Engineering and Mathematics (STEM) አካዳሚ፣ እና የአገረ-ገዢው የጤና ሣይንሶች አካዳሚ (Governor's Health Sciences Academy) - በACHS ውስጥም ይቀርባል።

## መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት - ለሁሉም ክፍት የሆኑ ዝግጅቶች (Open Houses) - ወደ ስድስተኛ ክፍል ለሚያድጉ ተማሪዎች

**ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 7፣ ከ9-10:30 a.m. (ጆርጅ ዋሽንግተን/George Washington መካከለኛ ደረጃ/Middle ትምህርት ቤት)**
**ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 21፣ ከ9-10 a.m. (ፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ/Francis C. Hammond መካከለኛ/Middle ደረጃ ት/ቤት)**
**ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 28፣ ከ9-10:30 a.m. (ጆርጅ ዋሽንግተን/George Washington መካከለኛ ደረጃ/Middle ት/ቤት)**
በኦገስት (August) 2023፤ በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎቻቸው ለሚጀምሩ - የወደፊት ወላጆች እና ቤተሰቦች፤ የ2023-24 የትምህርት ዓመትን እና ስለሚሰጡ ኮርሶች፣ ፕሮግራሞች፣ ዕድሎች፣ እርዳታዎች፣ እና የትምህርት-ክፍለ-ጊዜ ውጪ እንቅስቃሴዎች (extracurricular activitie) ምልከታ-እንዲያደርጉ ተጋብዘዋል።

## የ'All-City Fifth Grade Choral' ፌስቲቫል - የሚቀርብ-ዝግጅት

**አርብ፤ ፌብሩዋሪ (Feb.) 10 ቀን፣ ከ4-5 p.m.**
**ዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ-ደረጃ (5700 Sanger Ave)**
እንደ-እኛ የ'All-City Fifth Grade Choral' ፌስቲቫል ሆኖ ለመካፈል፤ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተመረጡ የአምስተኛ-ክፍል ተማሪዎች - ሙዚቃ ለማቅረብ መድረኩን ይወስዳሉ። በክፍላችን/division ውስጥ፤ በአይነቱ-የመጀመሪያ የሆነውን ዝግጅት-ለመካፈል፤ እባካችሁ ከACPS ጋር አብራችሁ-ተካፈሉ።

## የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮጀክት: የሚኔ ሃዋርድ (Minnie Howard) - የርቀት (Virtual) የማህበረሰብ ስብሰባ (በዙም/Zoom)

**ሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 13 ቀን፣ ከ6:30-7:30 p.m.**
የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) የካፒታል ፕሮግራም ቢሮ፣ የእቅድ-አወጣጥ እና ዲዛይን፣ ጊልባኔ ህንፃ (Gilbane Building) ኩባንያ - ወኪሎች፤ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮጀክት ላይ አዲስና-ማሻሻያ (update) ያቀርባሉ: ሚኒ ሃዋርድ መልሶ-ማልማት (Minnie Howard redevelopment)። በርቀት (virtual) የማህበረሰብ ስብሰባ መካፈል ካልቻላችሁ፣ በጊዜው ቀርቦ የነበረውን ገለፃ (presentation) በኦንላይን እንዲገኝ-የሚደረግ፣ እና የተቀበልናቸውን ሁሉንም የምላሽ አስተያየቶቻችሁ፣ በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ አግባብነት ካላቸው ሠራተኞች እና ውሣኔ-ሰጪዎች ጋር ይጋራሉ። እባካችሁን፣ ያላችሁን አስተያየት (feedback)፤ የCIP የግንኙነት-ክፍል ባለሞያ ለሆኑት - ለአርቴአ ፈንደርበርክ (Arte'a Funderburk ) - በartea.funderburk@acps.k12.va.us ላኩ።

## የፕሬዚዳንት ቀን (Presidents Day)

**ሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 20**
ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች፤ በ'ፕሬዚዳንት-ቀን/Presidents Day' ክብረ-በዓል ምክንያት፤ ዝግ-ይሆናሉ።

## የጆርጅ ዋሽንግተን - የልደት-ቀን ፐሬድ (George Washington Birthday Parade)

ሰኞ፣ ፌብሩዋሪ  (Feb.) 20 - ከ1-3 p.m.
በአገር-አቀፍ ደረጃ ትልቁ-የሆነው የጆርጅ ዋሽንግተን - የልደት-ቀን ፐሬድ (George Washington Birthday Parade) ሰልፍ-የሚካሄደው፤ ምርጫቸው አድርገው በተቀመጡበት ከተማ በኦልድ-ታውን አሌክሳንድርያ (Old Town Alexandria) መንገዶች ላይ ለአንድ-ማይል ርዝመት ይካሄዳል። ተጨማሪ-መረጃዎችን - መኪና ማቆሚያ፣ ካርታዎች/maps፣ ሰልፉ-የሚጓዝበትን መንገድ እና ሁኔታ ማወቅን-ጨማሮ ለማወቅ፤ በwww.washingtonbirthday.com ላይ ጎብኙ።

## መጪው - የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባዎች

**ሐሙስ፤ ፌብሩዋሪ (Feb) 16 ቀን፣ በ6:30 p.m.**
በመደበኛነት-የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ፣ ይካሄዳል።

**ሐሙስ፤ ፌብሩዋሪ (Feb) 16 ቀን፣ በ6:30 p.m.**
በመደበኛነት-የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ፣ ይካሄዳል። ይህ ስብሰባ፣ የትምህርት ቤት ቦርድን ለበጀት-ዓመት 2024 ያጸደቀውን በጀት - ማስፈጸምን ያካተተ ነው።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባዎች፤ በአካል-ተገኝቶ በትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ ክፍሎች ውስጥ - በ1340 Braddock Place ውስጥ - ሌላ ማስታወቂያ-ካልተሰጠ በስተቀረ፣ ይካሄዳል። የማህበረሰብ የህዝብ አባላቶች፣ በአካል-ተገኝተው (in person) ወይም በዙም/Zoom አማካኝነት፣ መሳተፍ ይችላሉ። በስብሰባ የጊዜ-ሰሌዳ ላይ ሊኖሩ ስለሚችሉ ማንኛውም አዲስና-ማሻሻያዎች (updates)፤ በትምህርት ቤት ቦርድ (School Board) ድህረ-ገጽ ላይ እባካችሁ - ጎብኙ።

## ቀኑን-አስታውሱ፤ እዳትረሱት: ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም (Equity for All Climate)፣ የዳሰሳ-ጥናት




በቀን-መቁጠሪያችሁ ላይ ሦስተኛውን ዓመታዊ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)ን ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም - ምን እንደሚመስል የሚያሳየውን (Equity For All Climate) የዳሰሳ ጥናትን፤ አርብ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 3 ቀን 2023 ላይ የሚጀመረውን እና እስከ እሁድ- ፌብሩዋሪ (Feb.) 26 ቀን 2023 ድረስ-የሚቆይ መሆኑን - ምልክት-አድራችሁ አስቀምጡ። የዳሰሳ-ጥናቱ፤ በ2025 Strategic Plan ውስጥ የተቀመጡት-ግቦችን ለመምታት - የእድገት-ሂደቱን የትምህርት ቤት ክፍሉ/school division - መቆጣጠር እንዲችል የሚረዳው-ነው።

ሁሉም የACPS ቤተሰቦች - ይህን የዳሰሳ-ጥናት ሞልተው እንዲያጠናቅቁ የሚበረታቱ እና፣ ስለ ትምህርት ቤት ክፍሉ (school division) - በተማሪ መማር፣ በማህበራዊ ስሜታዊ እርዳታ፣ በደህንነት እና ሌሎች ጠቃሚ-በሆኑ ነገሮች ዙሪያ - የትምህርት ቤት ክፍሉ (school division) ወደ ፍትሃዊ እኩልነት ያለው የመማሪያ አካባቢን ስለመማስገኘት በሚያደርገው ጥረቶች ላይ በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት የሚሰጡበት ነው። የዳሰሳ ጥናቱ፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ፣ በአረብኛ እና በዳሪ ቋንቋዎች ይቀርባል።

# ፌብሩዋሪ (February) የትምህርት ቤት ኮንፈረንሶች ቀናቶች እና ጠቃሚ-ጥቆማዎች




የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፤ በተማሪው የትምህርት ቤት ሕይወት እና በመኖሪያ-ቤት ሕይወቱ መካከል ያለውን አስፈላጊ-የሆኑ ግንኙነቶችን የሚፈጥር-ነው። ACPS፤ የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶችን፣ በየ-የትምህርት ዓመቱ የቀን-መቁጠሪያ ሁለት ጊዜ በማካሄድ፣ ቤተሰቦች እና አስተማሪች ስለተማሪዎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የእድገት-ሂደት ላይ ለመወያየት ዕድሎችን ይሰጣቸዋል።

በፌብሩዋሪ ውስጥ፣ የትምህርት ቤት ኮንፈረንሶች በሚካሄዱበት ጊዜ፣ እንደተለመደው የትምህርት ቤት የቀን-መቁጠሪያ ሆኖ - ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ለግማሽ-ቀን በእነዚህ የኮንፈረንስ ጊዜያቶች ወቅት ይማራሉ። በእነዚህ “ቀደም-ተብሎ በመለቀቂያ/early release” ቀናቶች ውስጥ፤ በሚከተለው የጊዜ-አቀማመጥ መሠረት - ተማሪዎች ከመደበኛው የመለቀቂያ-ሰዓት፣ ሁለት-ሰዓታት ቀደም ብለው የሚለቀቁ ይሆናል:

- በሁሉም ካምፓሶች ውስጥ የሚገኙ - የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 2 ቀን እና 3 2023 ላይ ከትምህርት ቤት፣ ከመደበኛው-ሰዓት - ሁለት-ሰዓታት ቀደም-ብለው የሚለቀቁ-ይሆናሉ።
- በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (elementary school) ውስጥ፣ ከPreK-8 እና ከK-8 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 9 ቀን እና 10 ቀን 2023 ላይ ከትምህርት ቤት፣ ከመደበኛው-ሰዓት - ሁለት-ሰዓታት ቀደም-ብለው የሚለቀቁ-ይሆናሉ።
- የመካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ በፌብሩዋሪ (Feb.) 16 ቀን እና 17 2023 ላይ ከትምህርት ቤት፣ ከመደበኛው-ሰዓት - ሁለት-ሰዓታት ቀደም-ብለው የሚለቀቁ-ይሆናሉ።

ለኮንፈረንሶቹ ስለመመዝገብ (sign-ups) በተመለከተ፤ እያንዳንዱ አስተማሪ - ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል።

ከወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ የበለጠ-ተጠቃሚ ለመሆን፤ የACPS፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ ማዕከል (Family and Community Engagement Center (FACE)፤ የሚከተሉትን በምክር-መልክ ያቀርባል:

- ተዘጋጁ (Get Ready): አብዛኛዎቹ የACPS ትምህርት ቤቶች፤ የ‘ParentSquare’ የጊዜ-ሰሌዳ የኮንፈረንስ ጊዜያቶችን ለቤተሰቦች ይጠቀማል። ቀልጣፋ እና ቀላል የምዝገባ ሂደት መኖሩን ለማረጋገጥ፤ በ‘ParentSquare’ አካውንታችሁ መመዝገባችሁን አረጋግጡ እና አፕ (app) ዳውንሎድ ማድረግዎን እርግጠኛ ሁኑ።
- ሁሉንም ሰው በአንድ-ገጽ ላይ እንዲመጣ-አድርጉ: ልጅዎ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ እና የአጠቃላይ ትምህርት አስተማሪ ካለው/ላት፤ ሁለቱም በኮንፈረሱ ውስጥ እንዲገኙና የተማሪዎ የእርዳታ ቡድን ግንኙነት እንዲያደርጉ መጠየቅ-ትችላላችሁ።
- ጥያቄዎችን ጠይቁ: የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - በአጠቃላይ ከ10-15 ደቂቃዎችን ይወስዳል። ከስብሰባው አስቀድማችሁ፣ ለአስተማሪው ማቅረብ የምትፈልጓቸውን ጥያቄዎች ዝርዝር አውጡ። አስፈላጊ-ከሆነ፣ በማንኛውም ጊዜ ማብራሪያ እንዲሰጣችሁ ለመጠየቅ አትፍሩ።
- ማስታወሻዎችን ውሰዱ: በኮንፈረንሱ ጊዜ፤ ቀናቶችን ፃፉ፣ የተጋሩ-ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እና የአስተማሪው ለጥያቄዎ-ሰጡትን መልስ ፃፉት።

- ልጅዎን ያሳትፉቸው — ከስብሰባው (በፊት እና በኋላ): አስቀድመው - ከልጅዎ ጋር ተነጋገሩበት፤ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ የሚወዱት የትምህርት-ዓይነት እና እንቅስቃሴ ምን እንደሆነ ጠይቁ፤ እንዲሁም፣ የማይወዱትስ ምንድነው፣ ለምን - ብላችሁ ጠይቁ። ከዚያ-በኋላም፤ ምን እንደተማራችሁ እና ከትምህርት ቤት ጋር ልጅዎን ወደ ስኬት እንዲደርስ ለመርዳት ምን-እንደምታቅዱ አጋሩ።

ብዙ የACPS ቤተሰቦች፤ በ'ParentSquare' ድህረ-ገጽ፣ በኢሜል ማገናኛ (email link፣ በቴክስት ማገናኛ (text link) ወይም በአፕ (app) ማስታወቂያዎች - አማካኝነት ወደ ኮንፈረንሶቹ ለመመዝገብ (sign up) ለማድረግ የሚችሉ-ይሆናል። እባክዎን፤ እነዚህን ደረጃ-በደረጃ የሚወሰዱ መመሪያዎችን አመላከቱ:
በEnglish (PDF) | en español (PDF) | አማርኛ (PDF) | بالعربية (PDF)

## በቅርብ ጊዜ የሚከናወን: ACPS - ለውጪ ፈቃድ-ያላቸው እጩዎች (Licensed External Candidates) - በፌብሩዋሪ (Feb.) 18 ቀን 2023 ላይ የ'Virtual Career Fair'ን ያዘጋጃል




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) የሰው-ኃይል አስተዳደር መምሪያ (Department of Human Resources (HR)፤ በዚህ የቅጥር-ወቅት በሆነው ሂደቱ ወደፊት-እየገባ ባለበት ጊዜ ላይ እያለ፤ የACPS የርቀት (Virtual) የስራ-መስክ ትዕይንት በፍጥነት-ጊዜው እየደረሰ ነው። ACPS - ፈቃድ-ያለው የስራ-ልምድ ትዕይንት (licensed career fair)ን  በርቀት/virtually (በዙም/Zoom አማካኝነት)፤ ቅዳሜ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 18 ቀን 2023 - ከ9 a.m. እስከ 2 p.m. ድረስ ያዘጋጃል። በዚህ ጊዜ ወቅት፤ እጩ-ሊሆኑ የሚችሉት - ከACPS ርዕሰመምህራኖች ጋር መገናኘት-የሚችሉ፤ እንዲሁም - ከACPS ጋር ቅጥር-ስለማግኘት ሁኔታዎች እየተወያዩ ባሉበት ጊዜ - ጎን-ለጎን - ስለ ክፍሉ (division) እና በየትምህርት ቤት ክፍሉ ያሉትን ስብጥር-ስላላቸው የተማሩዎች ቡድን - የበለጠ የሚያውቁም-ይሆናል።

በአሁኑ-ጊዜ ፈቃድ (license) ያላቸው እጩዎች ብቻ፣ ወይም እስከ ኦገስት (August) 2023 ፈቃዳቸውን ለማግኘት-ብቁ የሆኑ ብቻ፤ ለመካፈል ይችላሉ። ሁሉም-መሣተፍ የሚችሉ እጩዎች መመዝገብ ያለባቸው ሲሆን ይህም-ለርቀት የስራ-መስክ ትዕይንት (virtual career fair) በቅድሚያ-መመዝገብ አለባቸው።

ለቃለ-መጠይቅ የተመረጡ እጩዎች፤ የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘለትን የቃለ-መጠይቅ ሰዓቱን በኢሜል አማካኝነት የሚያገኙ እና የዙም ማገናኛ (Zoom link) ጋር - እስከ ሰኞ፣ ፌብሩዋሪ (Feb.) 13 ቀን 2023 ድረስ እንዲያውቁት-ይደረጋል።

## የፌብሩዋሪ (Feb.) 2 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



በፌብሩዋሪ (Feb.) 2 ቀን 2023 ስብሰባው ላይ፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ - የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ የሴት-ልጆች የቫሊቦል የስቴት ሻምፒዮና (Girls Volleyball State Championship) ቡድንን እውቅና-የሚሰጥ እና፣ የሚከተሉትን ርዕሶች በስብሰባ አጀንዳነት-ይዟል:

- ደህንነት እና የጥበቃ-ሁኔታ።
- የቴክኖሎጂ ዕቅድ።
- የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም (Capital Improvement Program (CIP) አዲስና-ማሻሻያ - ለሁለተኛው አጋማሽ።
- የበጀት ዓመት 2022 አጠቃላይ ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት (comprehensive annual financial report (CAFR)።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

## በጄንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ጄንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - መካከለኛ/medium ደረጃ ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤  በየ100,000 ሰዎች፣ 163.1 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በጄንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ-ይመለከታል።